የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 36
ADDIS ABABA 7th July, 2006


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፭፻/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ከአሜሪካን መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፬፻፴፱


**CONTENTS**


**Proclamation No. 500/2006**

The Government of United state of America Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation.... Page 3439


## አዋጅ ቁጥር ፭፻/፲፱፻፺፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአሜሪካ መንግሥት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የአየር አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአሜሪካ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸምን በተመለከተ ሕገ መንግሥታዊ ሥነ-ሥርዓቶች መፈጸማቸውን ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በዲፕሎማሲያዊ መንገድ እርስ በርሳቸው ካስታወቁበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 500/2006.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE BILATRAL AIR TRANSPORT SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF UNITED STATE OF AMERICA

**WHEREAS,** an Air Transport Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of United States of America was signed in Washington on 17th day of May 2005;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force on the date of the last notification of notes from either contracting parties confirming its ratification in accordance with its laws and regulation;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement on its meeting held on the 20th day of June, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2,30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ከአሜሪካን መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአሜሪካ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. በሚይ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዋሽንግተን ዲሲ ላይ የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት ፀድቋል።

**፫. <u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Government of United state of America Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation No.500/2006."

**2. Ratification of the Agreement**

The Bilateral Air Transport Services Agreement signed in Washington on the 17th day of May 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of United State of America, is hereby ratified.

**3. Power of the Minister of Transport and communication**

The Minister of Transport and communication is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**